የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ — ጥቅምት ፰ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 1
ADDIS ABABA – 19th October, 1995


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ........................ ገጽ ፹፭


### አዋጅ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፹፰

### የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤትን ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩· "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት" ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፫ መሠረት የተቋቋመ የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው ፤

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 2.30

## CONTENTS


Proclamation No. 13/1995
Establishment of the Secretariat of the House of Peoples' Representatives and of the House of the Federation Proclamation .............................. Page 85


### PROCLAMATION NO. 13/1995

### A PROCLAMATION TO ESTABLISH THE SECRETARIAT OF THE HOUSE OF PEOPLES' REPRESENTATIVES AND OF THE HOUSE OF THE FEDERATION OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

WHEREAS, it has become necessary to establish the Secretariat of the House of Peoples' Representatives and of the House of the Federation of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

*1. Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Establishment of the Secretariat of the House of Peoples' Representatives and of the House of the Federation Proclamation No. 13/1995.''

*2. Definitions*

In this Proclamation:

1) "the House of Peoples' Representatives'' means the House of Peoples' Representatives of the Federal Government established pursuant to Article 53 of the Constitution;


ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· "የፌዴሬሽን ምክር ቤት" ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፫ መሠረት የተቋቋመ የፌዴራሉ መንግሥት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፤

፫· "አፈ-ጉባዔዎች" ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፲፱) እና አንቀጽ ፷፪(፲፩) መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚመረጡ አፈ-ጉባዔዎች ናቸው።

፫· *መቋቋም*

፩· የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤቱ" ተብሎ የሚጠራ) ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጉዳዮችን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ሆኖ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጉዳዮችን በተመለከተ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ይሆናል።

፬· የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· ለምክር ቤቶቹ አካላት የጽሕፈት አገልግሎት ይሰጣል፤

፪· ለምክር ቤቶቹ ጠቅላላ ጉባዔና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች የሚያስፈልጉትን የመሰብሰቢያ አዳራሾች ያደራጃል፤

፫· የምክር ቤቶቹ አካላት ቃለ-ጉባዔዎች ፡ ውሳኔዎችና ሰነዶች በሚገባ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

፬· ለምክር ቤቶቹ አካላትና አባላት የቤተ መጻሕፍት ፡ የምርምርና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፡ በሚመለከተው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የሕግ ረቂቆችን ያዘጋጃል፤

፭· ምክር ቤቶቹ የሚያወጧቸውን መጽሔቶችና ጋዜጦች ሕትመትና ሥርጭት ይከታተላል፤

፮· የምክር ቤቶቹ እንግዶች አስፈላጊውን የመስተንግዶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፯· የንብረት ባለቤት ይሆናል ፡ ውል ይዋዋላል ፡ በስሙ ይከሳል፡ ይከሰሳል፤

፰· የምክር ቤቶቹን አካላት ሥራዎች ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፭· የጽሕፈት ቤቱ አቋም

ጽሕፈት ቤቱ፤

፩· በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጥ አንድ ኃላፊ ፤ እና

፪· አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

፮· የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

፩· የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ከአፈ-ጉባዔዎቹ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ይመራል፡ ያስተዳድራል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፡ ያስተዳድራል ፤

ሐ) የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባዔዎቹ ያቀርባል፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል ፤

መ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

2) "the House of the Federation'' means the House of the Federation of the Federal Government established pursuant to Article 53 of the constitution;

3) "Speakers'' means the Speakers respectively elected by the House of Peoples' Representatives and the House of the Federation pursuant to Article 55(19) and 62(11) of the Constitution.

3. *Establishment*

1) The Secretariat of the House of Peoples' Representatives and of the House of the Federation (hereinafter referred to as "the Secretariat'') is hereby established as an autonomous organ having juridical personality.

2) The Secretariat shall be accountable both to the Speaker of the House of Peoples' Represenatives and to the Speaker of the House of the Federation relative to matters falling under their respective jurisdiction.

4. *Powers and Duties of the Secretariat*

The Secretariat shall have the following powers and duties:

1) to provide secretarial services to the organs of the Houses;

2) to arrange for halls required for the general assemblies of the Houses and for the meetings of their various Committees;

3) to see to it that the minutes, decisions and documents of the organs of the Houses are recorded and kept properly;

4) to provide library, research and information services to the organs and members of the Houses; prepare draft legislation subject to instruction from the concerned organ;

5) to follow up the publication and circulation of periodicals and newsletters issued by the Houses;

6) to cause services of cordial reception to be extended to visitors to the Houses;

7) to own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

8) to perform such other duties as are conducive to the fulfilment of the activities of the organs of the Houses.

5. *Organization of the Secretariat*

The Secretariat shall have:

1) a Head to be elected by the House of Peoples' Represenatives; and

2) the necessary staff.

6. *Powers and Duties of the Head of the Secretariat*

1) The Head of the Secretariat shall, subject to general directives from the Speakers, direct and administer the activities of the Secretariat.

2) Without limiting the generality stated in sub-Article (1) of this Article, the Head of the Secretariat shall:

(a) exercise the powers and duties of the Secretariat specified in Article 4 of this Proclamation;

(b) employ and administer personnel of the Secretariat in accordance with the Federal civil service laws;

(c) prepare, and submit to the Speakers, the annual budget and work programme of the Secretariat, and implement same upon approval;

(d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work programme of the Secretariat;

ሠ) ጽሕፈት ቤቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤

ረ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለአፈ–ጉባዔዎቹ ያቀርባል፤

ሰ) ከአፈ–ጉባዔዎቹ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፫· የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ የበታች ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል። ሆኖም እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት እንዲሠራ የሚወክለው ኃላፊ ከ፴ ቀናት በላይ የሚሰራ ከሆነ ውክልናው በቅድሚያ ለአፈ–ጉባዔዎቹ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል።

፯· <u>የጽሕፈት ቤቱ በጀት</u>

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይፀድቃል።

፰· <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

፩· ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪· የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፱· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

(e) represent the Secretariat in all its dealings with third parties;

(f) prepare, and submit to the Speakers, reports on the activities and financial accounts of the Secretariat;

(g) perform such other functions as are assigned to him by the Speakers.

3) The Head of the Secretariat may delegate part of his powers and duties to subordinate officials and other employees of the Secretariat to the extent necessary for the efficiency of the Secretariat. However, in case of delegation to an official to act in his absence, for more than thirty (30) days, prior approval by the Speakers is required.

7. *Budget*

The budget of the Secretariat shall be approved by the House of Peoples' Representatives.

8. *Books of Accounts*

1) The Secretariat shall keep complete and accurate books of accounts.

2) The Secretariat's books of accounts and financial documents shall be audited, annually, by the Auditor General.

9. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 19th day of October, 1995.

Done at Addis Ababa, this 19th day of October, 1995.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE